# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

# የ2017 በጀት ዓመት

# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

| ማውጫ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ርዕስ | |
| 1 | መግቢያ | |
| 2 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ | 2 |
| 3 | በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና | 3 |
| 4 | ዓበይት ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎኖች | 21 |
| 5 | የ2017 በጀት የሰው ኃይል መግለጫ | 23 |
| 6 | የ2017 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈጻጸም | 24 |
| 7 | ማጠቃለያ | 25 |
| 8 | የ2017 በጀት ዓመት  አፈፃፀም በሠንጠረዥ | 27 |

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ (2016-2018) መሰረት በማድረግ የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም በመገምገም ዕቅዱ ተከልሶ ወደ ትግበራ ተገብቷል ። በዚሁ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ የዋና ዋና የተግባራት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል።

የ2017 በጀት ዓመት ውስጥ የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማለትም መግቢያ፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች፣ በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት እቅድ አፈጻጸም ትንተና እንዲሁም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የተወሰዱ መፍትሄ እርምጃዎች እና ማጠቃለያ በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ

መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ በጥራት መንደር ዉስጥ ደረጃቸውን የጠበቁ ስድስት የወርክሾፕ፣ የላቦራቶሪ እና የአስተዳደር ህንጻዎች ተገንብተውለት ወደ ስራ ተገብቷል። በተጨማሪም በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በአለም ባንክ ብድር የተለያዩ መሳሪያዎች የተገዙ በመሆናቸው የሥነ-ልክ ተቋምን አቅም በማሳደግ ለአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ስኬት ከምርታማነት ጥራትና ተወዳደሪነት አንፃር ኢንስቲትዩቱ አይነተኛ ሚናውን እንዲጫወት ያደርጋል።
በዚሁ አግባብ ኢንስቲትዩቱ በማቋቋሚያ ደንቡ የተሰጠውን ተልዕኮ ግምት ውስጥ በማስገባት የምርምር፣ የስልጠና፣ የማማከር እና ቴክኒክ ድጋፍ፣ በጥናትና ምርምር የተደገፉ የካሊብሬሽን እና የጥገና አገልግሎቶችን የመስጠት ሃላፊነቱን በብቃት እየተወጣ ይገኛል።

በሌላ በኩል ህዳር 2016 ዓ.ም ባለ 8 እርከን የጥናትና ምርምር ተቋም መሆን ያስቻለው አደረጃጀት በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የጸደቀለት በመሆኑ በዚሁ አግባብ ምደባ ተከናውኗል። ሆኖም የተመደቡት ሠራተኞች የኢንስቲትዩቱን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት በቂ ባለመሆናቸው ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጥያቄ በማቅረብ እና በማስረዳት 20 የሚደርሱ የዘርፉ ተመራማሪዎችንና ሰራተኞችን ለመቅጠርም ፍቃድ የተሰጠን በመሆኑ የቅጥር ሂደቱ በሂደት ላይ ይገኛል። የሰው ኃይል አቅማችንን ከማጎልበት

አንጻር  በበጀት ዓመቱ ለ211 ሠራኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለአንድ ወንድ ሠራተኛ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል፡፡
የሀብት አጠቃቀም በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ የበጀት አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ እንዲሁም በውስጥ ኦዲት የክትትል ስራዎች የሚሰሩ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት እና የ4ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት የ1ኛ ፣ የ2ኛ እና 3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡ ከለውጥና መልካም አስተዳደር አንጻር ለተገልጋዮች የቅሬታ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርአት የተዘረጋ በመሆኑ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በየደረጃው የመፍታት ስራ ተሰርቷል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ አገልግሎታችንን ለደንበኞች ምቹ እና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር በአዲሱ ህንጻ ላይ የደንበኞች አገልግሎቱን ምቹ ለማድረግ የተሰራ ሲሆን በአለም ባንክ ብድር በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ አዳዲስ የኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ለማድረግ የካሊብሬሽን አገልግሎት እና የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና አገልግሎትን በከፊል በኦንላይን ለደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል፡፡

## 3. በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና

**የተግባራት አፈፃፀም**
አጠቃላይ የኢንስቲትዩቱ የ2017 በጀት ዓመት የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም **94.5%** ነው፡፡

**ግብ 1፡ የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ (ክንዉን 88%)**

**1.1ጥናትና ምርምር ማካሄድ (ክንዉን 95%)**

**1.1 ጥናትና ምርምር ማካሄድ (ክንውን 95%)**

ሁለት ጥናት እና ምርምር ለማካሄድ ታቅዶ

- ✓ Completion of the Review by Implementation in Excel of mass calibration using orthogonal design  የጹሑፍ ስራው ተጠናቋል፡፡
- ✓ በቮልቴጅ መዋዠቅ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚታደግ ዲቫይስ ቅድመ ፕሮቶታይፐ ፍተሻዎችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ የዲዛይን ሥራ ተጠናቆ በሙከራ ሂደት ላይ ይገኛል (ክንውን 95%)፡፡

## 1.2. የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 93%)

1.2.1 34000 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ በመካኒካል ሥነ ልክ ላቦራቶሮች:- የግዝፈትና ይዘት 12,135 ፣ የኃይልና ግፊት 2962 ፣ የዳይሜንሽን 2060 እንዲሁም በኤሌክትሮ ማክግኔትክ ሥነ ልክ ላብራቶሮች፡- በሙቀት 11251፣ በኤሌክትሪካል 562 እና በቅርንጫፍ ላብራቶሪ 2772 በድምሩ 31,742 የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የነዳጅ ዋጋ መጨመር ምክንያት በማድረግ በርካታ የመንግስት እና የግል ድርጅቶች የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከር ካሊብሬሽን ጥያቄ በማቅረባቸው በበጀት ዓመቱ 3 ሚሊዮን ሊትር ገደማ ተሰርቷል (ክንውን 93.4%)፡፡

## 1.3. የጥገና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 80%)

1.3.1 ለ350 መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ከህክምና ውጭ ለሆኑ የሣይንስ መሣሪያዎች 194፤ የህክምና የሣይንስ መሣሪያዎች 88 በድምሩ ለ 282 መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 80%)፡፡

**1.4የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 100%)፡፡

1.4.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች 8 ስልጠናዎችን ለመስጠት ታቅዶ፡-

- ከ USP ጋር በመተባበር
  - ✓ ለ98 (ሴት= 36 ወንዶች= 62) ከተለያዩ ክልሎች ለተመረጡ የባዮሜዲካል መሐንዲሶች በCold chain equipment and General Metrology ላይ በሀዋሳ፣አዳማ እና ድሬደዋ የጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ተሰቷቸዋል፡
  - ✓ ለ8(ሴት=1 ወንዶች=7) የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትየት ባለሙያዎች በርስበርስ ንጽጽር ፕሮግራሞች ላይ ለ2 ቀናት በአዳማ የጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡
- ለ13 የአየር ኃይል ወታደራዊ አመራር እና የሰራዊት አባላት በጀነራል ሜትሮሎጂ ፣ በኤሌክትሪካል ስነ-ልክ እና በISO/IEC 17025 የፅንሰ ሃሳብ እና የተግባር ስልጠናዎች በደብረዘይት አየር ኃይል ቅጥር ጊቢ ለ15 ቀናት ተሰጥቷል፡፡

- ከሸገር ከተማ አስተዳደር ከ 12 ቱም ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ ለ117 (ወንዶች=60 ሴቶች= 57) የንግድ ቢሮ አመራሮችና ቡድን መሪዎች በህጋዊ ስነልክ ፣በሚዛን መስፈሪያ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ዙሪያ የሁለት ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥታል፡፡
- ከአዲስ አበባ ተግባረእድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የ legal metrology ስልጠና በ volume, mass, balance, dimensional and pressure የተግባር ስልጠና ለ23 ተማሪዎች ተሰጥታል፡፡
- ከኦሮሚያ ጤና ቢሮ እና ከኦሮሚያ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ለ ለ27( ወንድ= 25 ሴት =2) እንዲሁም ከደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ ጤና ኮሌጅ ለመጡ 2 ወንዶች በጠቅላላው ለ29( ወንድ=27 ሴት=2) ባዮ ሜዲካል መሐንዲሶች በ Analogue electronics, Digital electronics , and power supply ላይ በሁለት ሳምንት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከጤና ሚኒስትር ጋር በመተባበር በተደረገ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ለ28 (ሴ=3, ወ=25) Biomedical Engineers and Technicians በተግባረእድ ቴክኒካል ኮሌጅ በኤሌክትሮኒክ ቦርድ ጥገና ላይ የጽንሰ ሀሳብ እና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በ AHRI አስተባባሪነት በደብረዘይት አሻም አፍሪካ ሪሶርት በተዘጋጀ መድረክ ላይ ከተለያዩ ምርምር ተቋማት ለመጡ 30 (ወንድ=12 ሴት=18) ተመራማሪዎች ስለ prototyping and calibration የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

1.5 **የቴክኒክ ድጋፍ እና ምክር አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 100%)፡፡

1.5.1. *ሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለህጋዊ ሥነ-ልክ፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ የግል ባለሃብት ወ.ዘ.ተ ጥያቄ ለሚያቀርቡ 100% የቴክኒክ እና የምክር አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ፡-*

- ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ቀደም ሲል በተዘጋጀላቸው የመለኪያ መሳሪያዎች ግዢ ዝርዝር መስፈርት /Specification/ መሰረት ስለመቅረባቸው የኢንስፔክሽን ስራ ተሠርቷል፡፡
    - ለኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ አቅርበውየመግቢያ መረጃ ተጠናክሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡
    - የማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ግዢ መፈጸም የሚያስችል በ volume, mass, balance, force and pressure ቴክኒካል ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቷል፡፡
    - ከሥነልክ ቡድን ጋር ለሁለት ቀን የልምድ ልውውጥ ተደርጓል ፡፡

- ➢ OSE(ኦሮሚያ ሲድ ኢንተርፕራይዝ) የላቦራቶሪ እቃዎች ግዥ የቴክኒክ ግምገማ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ➢ ከጤና ጥበቃ ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተዘጋጁ
  - medical device roadmap
  - guideline for medical device maintenance
  - Medical device management strategy ዶክመንቶች ላይ 4 መሀንዲሶች በማሳተፍ እገዛ አድርገናል (ክንውን 100%)፡፡

1.6 **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 0%)፡፡

1.6.1 ለ100% የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውን 0%)፡፡ ያልተከናወነበት ምክንያት ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር አገልግሎቱን መስጠት እንድንችል ደብዳቤ ተጽፎ ክትትል በመደረግ ላይ ነው ፡፡

1.7 **የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ** (ክንውን 100%)፡፡

1.7.1. የውጭ ተገልጋይ እርካታ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ አዲስ አበባና አካባቢው በደብረ ብርሃን፣ሞጆ፣ ሱሉልታ ፣ ሆለታ፣ ሰበታ፣ ጅማ፣ ሀዋሳ እና አዳማ ላሉ ደንበኞች መጠይቅ በማዘጋጀት የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የእርካታ ደረጃ 90% ውጤት ተመዝግቧል (ክንውን 100%) ፡፡

**ግብ 2፡ ተደራሽነትን ማሳደግ (ክንውን 97.2%)**

**2.1 በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋትና ማስቀጠል (ክንውን 100 %)**

**2.1.1** በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት በጅማ እና ባህር ዳር ቅርንጫፍ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ በጅማ እና ባሕርዳር ቅርንጫፎች በእርጥበት (Grain Moisture) መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር ተችሏል (ክንውን 100%)

## 2.2 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ (ክንውን 93.75%)

2.2.1 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት የኢንስቲትዩቱን ድህረ ገጽ 24/7 ደህንነቱን መጠበቅ እና ለደንበኞች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ

- አየር ላይ ያለው የነባሩን ድረ ገጽ ደህንነት የመጠበቅ እና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ክትትል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የኢንስቲቱዩቱን ዌብሳይት አሁናዊ የተቋሙን ሁኔታ ያገናዘበ መረጃ እንዲኖረው መረጃዎች እንዲከለሱ ድጋፍ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

2.2.2 ለዌብሳይት ተጠቃሚዎች ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ ተዘጋጅተው በተቋሙ የፌስ ቡክ ገጽ ላይ አየር ላይ የዋሉ ሁሉም ዜናዎች በድረ ገጹ ላይ እንዲጫኑ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

## 2.3. የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት (ክንውን 100%)፡፡

2.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ለማካሄድ ታቅዶ የንግድና ቀጠናዊ ትብብር ሚኒስቴር ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመተባበር ባዘጋጀው መድረክ ላይ ለህጋዊ ሥነ- ልክ ተቆጣጣሪ አካላት እና ከድሬዳዋና ሃረማያ ዩኒቨርስቲ ለተውጣጡ መምህራኖች በድሬዳዋ እና በሀዋሳ ከተሞች ስለ ኢንስቲትዩቱ ስልጣን እና ተግባር እንዲሁም በምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሠጥቷል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሲቪክ ማህበረሰብ ደርጅት አመራርና ሰራተኞች እና የቦሌ ሃይስኩል ተማሪዎች ለጉብኝት መጥተው ስለ ተቋማችን በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

## ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ (ክንውን 99%)፡፡

### 3.1 የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት እና የበጀት አጠቃቀም መከታተል (ክንውን 92%)፡፡

3.1.1. የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% ለመጠቀም ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ተጨማሪ በጀት ብር 72,904,683 ለመደበኛ በጀት ተጨማሪ በማስፈቀድ 99.3% መጠቀም ተችሏል፡፡ የካፒታል በጀት ለውጪ ግዢ ኤልሲ የተከፈተበትን ብር 57,770,289 ጨምሮ 99.9% መጠቀም ተችሏል፡፡ የ2017 በጀት ዓመት መደበኛና ካፒታል በጀት ብር 225,043,971 ተፈቅዶልን 224,076,712 99.5% መጠቀም ተችሏል፡፡

**3.2. የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ** (ክንውን 100%)፡፡

3.2.1. 15,000,000 የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ከካሊብሬሽን አገልግሎት፣ ብር 14,778,110.95 ከሳ.መሳ.ጥገና አልግሎት ገቢ ብር 240,041.33 በአጠቃላይ ብር 15,018,152.28 ገቢ ተሰብስቧል (ክንውኑ 100%)፡፡

**3.3 የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** (ክንውኑ 100%)፡፡

- የ2016 በጀት ዓመት የፊስስ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የ2016 በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት፣
- የ2017 በጀት ዓመት የ1ኛ ፣ የ2ኛ እና 3ተኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተልኳል ፡፡ እንዲሁም በተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ክዋኔ ኦዲት ተሰርቷል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 4. የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** (ክንውን 100%)፡፡

**4.1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ** (ክንውን 100%)፡፡

**4.1.1** አጋር ድርጅቶችን ስትራቴጂካዊ አስተዋጽኦ ለማሳደግ ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ ታቅዶ

- ለኬሚካል ሥነ-ልክ ምርምር የሚሆን Gap identification and need an intervention in collaboration with KOICA Project ተዘጋጅቷል ፡፡ እንዲሁም በ PTB ኘሮጀክት ስልጠና ለማግኘት አሰልጣኞች ተለይተዉ ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡
- ለ2018 በጀት ዓመት የካሊብሬሽን አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማሻሻያ ጥናት ፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ ተዘጋጅቷል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 5. አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** (ክንውን 102%)፡፡

**5.1 ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት** (ክንውን 100%)፡፡

**5.1.1** በሥነ-ልክ ዘርፍ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለመጠበቅ ታቅዶ በሙቀት እና በኤሌክትሪካል የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተጠብቋል፡፡ እንዲሁም በሀይል (50 KN, 100KN, 250KN, 5000KN) እና በግፊት(Digital prssure gauge) ከደቡብ አፍሪካ የሥነ ልክ ተቋም የእርከን ተዋረድ ትስስር ተጠብቋል (ክንውን 100%)፡፡

5.1.2 በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለማሰራጨት ታቅዶ በውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) በሙቀት እና በኤሌክትሪካል የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ጊዜያቸዉ የደረሰ ማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም በሁሉም ላቦራቶሪዎች ውስጥ ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተጠብቆላቸዋል (ክንውን 100%)፡፡

**5.2 ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል** (ክንውን 90.4%)፡፡

**5.2.1** ዕዉቅና በተገኘባቸዉ (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

**5.2.2** ዕዉቅና ባልተገኘባቸው የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ እና ማስተካከያዎችን ለማከናወን ታቅዶ በወበቅ፣ በዕርጥበት፣ በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ፣ በጊዜ እና በድግግሞሽ እንዲሁም በኃይል(On site Force calibration),ይዘት (ታንከር) ,በግፊት (On site Pressure calibration) and Dimensional የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን ተችሏል (ክንውን 100%)፡፡

**5.2.3** በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የተቋረጡ የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት እና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ

- (የኤሌክትሪካል እና የሙቀት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት በISO/IEC 17025 ጥራት ኦዲት ተደርጎ እውቅናውን ማስቀጠል ተችሏል፡፡ እንዲሁም በግዝፈት የአለካክ መስክ እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ዝግጁ በማድረግ እና በDAkkS Assessment/ ግምገማ / በተሳካ ሁኔታ በማካሄድ እውቅናው ተመልሷል፡፡
- በይዘት አለካክ መስክ በDAkkS Assessment/ ግምገማ / በተሳካ ሁኔታ በማካሄድ እና NC Clear ተደርጎ ውጤቱን በመጠበቅ ላይ እንገኛለን (ክንውን100%)፡፡

5.2.4 በሁሉም ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች የግዝፈት እና የሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ የሃዋሳ እና ጅማ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች የግዝፈት እና የሚዛን እንዲሁም የርጥበት ካሊብሬሽን አገልግሎቶች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ተከናውኗል (ክንውን 40%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በቀሪዎቹ 3 ቅርንጫፎች የሚቀር በመሆኑ ነው፡፡

5.2.5 የውስጥ ጥራት ኦዲት በተካሄደባቸው የአለካክ መስኮች በ ISO/IEC 17025 የጥራት ሥራ አመራር የአሰራር ሥርዓት መሰረት የስራ አመራር ግምገማ /Management Review/ ለማካሄድ ታቅዶ የውስጥ ጥራት ኦዲት በተካሄደባቸው የአለካክ መስኮች በ ISO/IEC 17025 የጥራት ሥራ አመራር የአሰራር ሥርዓት መሰረት የስራ አመራር ግምገማ /Management Review/ ተካሂዷል (ክንውን100%)፡፡

5.2.6 በተካሄደው የውስጥ ጥራት ኦዲት ግኝት መሰረት የእርምት እርምጃ መውሰድ እና ማስተካከያዎችን በማከናወን ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ በተካሄደው የውስጥ ጥራት ኦዲት ግኝት መሰረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ እና ማስተካከያዎችን በማከናወን ሪፖርት በሐምሌ ወር መጀመሪያ አካባቢ ይጠቃለላል (ክንውን100%)፡፡

5.3. **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** (ክንውን100%)፡፡

5.3.1 ከ ጀርመን እውቅና ሰጭ ተቋም (DAkkS) በተገኘ የሚዛን ካሊብሬሽን እውቅና መሰረት ለሁለት ቅርንጫፍ ላቦራቶሪ ሰራተኞች የCompetency training በመስጠት እና በማብቃት ዓለም ዓቀፍ እውቅና ያለው የካሊብሬሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ታቅዶ ለደሴ፣ ለሐዋሳ፣ ለባህርዳር እና ጅማ ቅርንጫፎች የሚዛን ካሊብሬሽን እውቅና መሰረት የCompetency ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ለድሬደዋ ቅርንጫፍ በይዘት አለካክ ላይ Onsite ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

5.3.2 በቀጣይ ዓለም አቀፍ ዕዉቅና የሚጠየቅባቸው (የጨረራ፣ የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እና የኬሚካል) የአለካክ መስኮች የልኬት ወሰን ለመለየት ታቅዶ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ የአለካክ መስክ (Calibration of wave Length) ላይ የልኬት ወሰን ተለይቷል፡፡ እንዲሁም በ Organic Inorganic Chemistry ስር ያሉ መሳሪያዎችን ኢንስቶል ለማስደረግ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው (ክንውን 100%)፡፡

5.4 **በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ** (ክንውን 125%)፡፡

5.4.1 በ2 ኤሌክትሪካል የአለካክ መስክ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 3 የላብራቶሪዎች የመለካት አቅም ማስመዝገብ ተችሏል (ክንውን 150%)፡፡

5.4.2 በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ ለማስመዝገብ ታቅዶ በይዘት ዘርፍ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/) ለማስመዝገብ ተችሏል (ክንውን 100%)፡፡

5.5 **ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ**(ክንውን 100%)፡፡

5.5.1 ከዓለምአቀፍ (BIPM) ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ለማመቻቸት ታቅዶ 17ኛው የAFRIMETS GA ስብሰባ ከጁላይ 29 እስከ ኦገስት 02 ቀን 2024 በሙቀት በonline እና በኤሌክትሪካል በአካል ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ ተሳትፎ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም ከሩዋንዳ (RSB) ጋር በይዘት ዘርፍ (Small Volume Measurements) እና በኃይል አለካክ መስክ በኬኒያ በተዘጋጀው በ100 kN፣200 kN እና 2000 kN የንጽጽር ፕሮግራም በማካሄድ ሪፖርትም ቀርቧል (ክንውን 100%)፡፡

5.6. **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 100%)፡፡

5.6.1 የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት አደረጃጀት ለዉጥ ምክንያት በISO 17025:2017 የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት Quality manual ለመከለስ ታቅዶ በISO 17025:2017 የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት Quality manual ተከልሶ በጀርመን እውቅና ሰጭ ተቋም (DAkkS) ተገምግሞ ተጠናቋል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 6. የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** (ክንውን 87.5%)፡፡

**6.1. የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ** (ክንውን 87.5%)፡፡

6.1.1 በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ F1 ወደ E2 ደረጃ ለማሳደግ የካሊብሬሽን ስራ ማስጀመር እና የቅድመ ዕውቅና ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

**6.1.2** በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration, frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ የስልጠና ቢጋር (TOR) ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ በcentrifuge calibration ላይ በራስ ባለሙያ በማንበብ ስልጠና በመስጠት ስራ ተጀምሯል (ክንውን 50%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በተዘጋጀው ቢጋር መሰረት (TOR) ስልጠና ባለመገኘቱ ነው፡፡

**6.1.3** በኬሚካል ስነ-ልክ የአለካክ መስክ በReference materials production and primary pH laboratories ስራ ማስጀመር እና የቅድመ ዕውቅና ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ የአናላቲካል መሳሪያዎችን ኢንስቶል ለማስደረግ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

- ለ3 የናሙና ዝግጅት መሳሪያዎች ወርክ ኢንስትራክሽን ተዘጋጅቷል፤ በprimary pH standard lab ስራ ለማስጀመር የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እና ኬሚካሎች ግዢ ተከናውኗል፡፡
- የላቦራቶሪዎች የኤሌክትሪክ እና የሃይል መጠን ለመሳሪያዎች በመስፈርት መሰረት ተስተካክሎ እንዲቀየር እና የጀኔሬተር መስመር ኢንዲገናኝ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**6.1.**4 በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ በፎቶሜትሪ /photometer/ የአለካክ መስክ በኢንስቲትዩቱ አማካሪ በዶ/ር ፍራንዝ አማካኝነት ስልጠና በመዉሰድ የካሊብሬሽን አገልግሎት ተጀምሯል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 7. የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል (ክንውን 94%)፡፡**

**7.1. የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 73.75%)፡፡

7.1.1 የኢንስቲትዩቱን የካሊብሬሽን አገልግሎትን በከፊል ኦንላይን ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የካሊብሬሽን ሰርተፍኬትን የኦንላይ አገልግሎት በከፊል እና የተደራጀ መረጃ አያያዝ ላይ እየተሰራ ነው (ክንውን 30%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የህንጻዎች ኔትወርክ ባለመጠናቀቁ ምክንያት በከፊል በላብራቶሪዎች ተጀምሮ የነበረው የካሊብሬሽን ኦላይን ሲስተም አገልግሎቱ በመቋረጡ ነው፡፡

**7.1.2** የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና አገልግሎትን በከፊል ኦላይን ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ከሚመለከታቸው ስራ አስፈጻሚ ጋር በጋራ በመሆን የተሰራውን ፖርታል ተገምግሞ ዲፕሎይመንት ተጠናቋል፡፡ የኢንሳ ኦዲት ስራ ሲጠናቀቅ ስልጠና በመስጠት ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡ (ክንውን 95%)፡፡

**7.1.3** የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ከሚመለከታቸው ስራ አስፈጻሚ ጋር በጋራ በመሆን የተሰራውን ፖርታል ተገምግሞ የመጨረሻ ዲፕሎይመንት ተጠናቋል፡፡ የኢንሳ ኦዲት ስራ ሲጠናቀቅ ስልጠና በመስጠት ስራ ላይ የሚውል ይሆናል (ክንውን 80%)፡፡

**7.2 ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ** (ክንውን 91.67 %)፡፡

**7.2.1** በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ለማስጠበቅ ታቅዶ በመደበኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በጣልቃገብ፤በይግባኝ እና በአፈጻጸም የቀረቡ ጉዳዮች ክርክር ተደርጎባቸው፤ ውሳኔ አግኝተዋል (ክንውን 100%)፡፡

**7.2.4** ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ለማድረግ ታቅዶ የተቋሙ የሥነ ምግባር መመሪያ ወይም ኮድ ላይ አስተያየት በመስጠት የህግ ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**7.3.** የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም **(ክንውን 100%)**

7.3.1 በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ለማጠናቀቅ ታቅዶ አብዛኛዎቹ የአገር ውስጥ ግዥዎች በመጠናቀቅ ላይ ሲሆኑ የውጪ ግዢ ኤልሲ ተከፍቶ ከአቅራቢው ድርጅት ጋር ውል ተፈፅሟል (ክንውን 100%)፡፡

**7.4 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** (ክንውን 100%)

7.4.1 በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በዓይነታቸው ለመለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ለማድረግ ታቅዶ

- የኢንስቲትዩቱ በርካታ ንብረቶች ተለይተውና ተደራጅተው ዋጋቸው ተገምተው በተለያዩ ጊዚያት ለመቂዶንያ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ ለተግባረዕድ ት/ቤት፣ ለመድኃኔአለም ት/ቤት፣ ለአፋር መስተዳድር በስጦታ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የኮተቤ ቢሮዎች እና በርካታ ንብረቶች ካርታ እና ሰነድን ጨምሮ ከኢትዮጵያ ነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን ተወካዮች ጋር በመሆን በመመዝገብ በቃለ ጉባዔ ለባለስልጣኑ ርክክብ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 8. ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** (ክንውን 87.5%)፡፡

**8.1 ከጥራት መሰረተ ልማት፣ ከከፍተኛ ትምህርትና ከምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 85.7%)፡፡

8.1.1 እስከ 32 ለሚደርሱ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለሚመጡ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ለማካሄድ ታቅዶ

- ከወራቤ ዩኒቨርሲቲ ለመጡ የፊዚክስ ዲፓርትመን ሃላፊ ለ2 ሳምንታት የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ተካሂዷል ፤
- ከተግባረዕድ ቴክኒክ እና ሞያ ለመጡ የሕጋዊ ስነ-ልክ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ተካሂዷል ፤
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፊዚክስ ዲፓርትመንት ለመጡ 8 ተማሪዎች ለ6 ወራት የሚቆይ ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም በመሰጠት ላይ ነው፡፡ እንዲሁም ቁጥራቸው 49 ለሆኑ የተግባረዕድ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች እና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመጡ ተማሪዎች በግዝፈት፣ይዘት እና ግፊት መስክ ኢንተርንሺፕ ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

**8.2 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 100%)፡፡

**8.2.1** በበኬሚካል ስነ-ልክ የአለካክ መስክ በReference materials production ከ(NMISA) and primary pH Standards ከKRISS laboratories ጋር ስራ የማስጀመር ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ ከ PTB እና KOICA ፕሮጀክት በሚገኝ በጀት ስልጠና ለማግኘት ዕቅድ ተይዟል የመሳሪያዎች ለኢንስታሌሽን ተጀምሮ እየተከናወነ ነዉ፤ ከ PTB እና UNIDO ጋር የ pH

ላቦራቶሪን ስራ ለማስጀመር የሚያስችል የስራ እቅድ እና የአሰልጣኝ ምልመላ ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

**8.3 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት (ክንውን 100%)፡፡**

8.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዶ

- የፎቶሜትሪ እና ራዲዮ ሜትሪ ሥነ-ልክ ዴስክ ከኢትዮጵያ ተስማሚነት እና ድርጅት (ECAE) workshop በጋራ የመጠቀም እና ልምድ የመለዋወጥ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት (IES) የተለያዩ ደረጃዎች ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፣ እንዲሁም በአምስት ደረጃዎች ላይ በዎርኪንግ ግሩፕ ዉስጥ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡
- ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ጋር በትብብር ስራ ተሰርቷል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ (ክንውን 94.4%)፡፡**

**9.1 የሰው ሀብት ልማት ማልማት (ክንውን 100 %)፡፡**

9.1.1. ለ125 ሠራተኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ

- የሙቀትና ወበቅሥነ-ልክ /Temperature and humidity for assistance researcher and laboratory technician ፤Basic pressure training based on DKD R-1 and calibraition on material testing equipment based on ISO 7500-1 ለ 25(ወ =21 ሴ= 4) ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ISO 17025 General Competence of Testing and Calibration Equipment Handing ለ23 (ወ=18 ሴ=5) ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በሞስቸር/እርጥበት/ ፣በአኮስቲክ እና በቫይብሬሽን ዙሪያ ለ14 (ወ=13 ሴ=1) ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በንብረት አስተዳደር ዙሪያ 42 (ወ=27 ሴ=15) ሠራኞች ስልጠና ወስደዋል፡፡
- ለ11 (ሴ=3, ወ=8) የሙቀትና ወበቅ ሥነ-ልክ ምርምር ዴስክ ተመራማሪዎች ለ10 ቀናት የጽንሰ ሃሳብ እና የተግባር ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡
- Effective & Efficient Time managemetnt ላይ ለ34(ሴት=13, ወንድ=17) ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለ15 የኢንስቲትዩቱ አዲስና ነባር ባለሙያዎች በኃይል ና በግፊት አለካክ የጽንሰ ሀሳብ እና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ለ8 ( ሴቶች= 3 ወንዶች= 5) የሙቀትና ወበቅ ሥነ-ልክ ምርምር ዴስክ ተመራማሪዎች ለ10 ቀናት የጽንሰ ሃሳብ እና የተግባር ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡
- ለመካኒካል ሥነ-ልክ ምርምር ዴስክ ተመራማሪዎች በ5 አይነት ዘርፎች (mass, volume, balance፣ ISO/IEC 17025 and ethics related fields) ለ9 (ወ=6 ሴ=3 ) ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡
- አዲሱ የንብረት አስተዳደር አዋጅ 12333/2016 ለ34 (ሴት=6, ወንድ=28) በውስጥ አቅም ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ለ211 (ሴት=53, ወንድ=158) ሰራተኞች በተለያዩ የስልጠና ዘርፎች ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

**9.1.2** ለአንድ ሰራተኛ በሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ለመስጠት ታቅዶ ለአንድ ወንድ ሰራተኛ የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

9.2. **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መከታተልና ማጠናከር** (ክንውን 79.7%)፡፡

9.2.1 ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት 19,495 ብር ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 18,735.59 ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ደመዎዛቸው አነስተኛ ለሆኑ 49(ወ= 34 ሴ= 38) የኢንትስቲትዩቱ ሠራተኞች የአዲስ ዓመት በዓል መዋያ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን አስተባባሪነት በመቅዶንያ አረጋውያን መረጃ ማዕከል በመገኘት ማእድ ለማጋራት የ 93,750 ብር አስተዋጽኦ ተደርጓል (ክንውን 95.8%)፡፡

9.2.2 ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶችን በማፈላለግ የተቋሙን ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ከአምዴ ማማ ድርጅት ጋር በመተባበር ለ5 ሴት ሰራተኞች የ3 ሳምንት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ስልጠናውም በማያገለግል ወረቀት ጌጣጌጥ መስራት በመሆኑ በትርፍ ሰዓታቸው እየሰሩ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም አገልግሎት ላይ የዋሉ ወረቀቶችን በማሰባሰብ ከአንዴ ማማ ድርጅት ጋር በመተባበር ገቢ የሚገኝበት ስራ ተሰርቶ 35 ሺህ ብር በሴቶች ፎረም አካውንት ገቢ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

9.3 **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 100%)፡፡

9.3.1 በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የስነምግባር መመሪያ ለማጠናቀቅ፣ ታቅዶ የሥነ-ልክ የካልብሬሽን አገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር

የውስጥ መመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል እንዲሁም ለተቋሙ አመራርና ሠራተኞች የስነምግባር መመሪያ ሰነድ ተዘጋጅቷል በበላይ አመራሩም ፀድቋል፡፡ (ክንውን 100%)፡፡

9.3.2 በተቋሙ በህግ ሀብት ማስመዝገብ የሚገባቸው ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ለመከታተል ታቅዶ 177 (ወ=107 ሴ=70) አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል (ክንውን 98%)፡፡**

**10.1 የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ (ክንውን 100%)፡፡**

**10.1.1** የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፓርት ለማቅረብ ታቅዶ የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአካባቢው የሚያመነጨውን መጠን በሳምንት አንድ ጊዜ የሰርቪሊያንስ ስራ እየተስራ ይገኛል(ክንውን 100%)፡፡

**10.2 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት (ክንውን 100%)፡፡**

10.2.1. የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ

- ለ15 ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ እና ለ17 ተሽከርካሪዎች ጥገናና ሠርቪስ ተደርጓል ፡፡
- ለአንድ ተሽከርካሪ ኖርማላይዜሽን/በሊትር ተሽከርካሪው የሚጓዘው ኪሎ ሜትር መረጃ በአንበሣ አውቶብስ ድርጅት ተሰርቷል፣
- ከገንዘብ ሚ/ር የተሰጠንን የሃይውንዳይ ተሽከርካሪ የዲክላራሲዮን፣ የቦሎ፣ የታርጋና የሊብሬ ኘሮሰስ ተጠናቋል፣
- አዲስ ለተመደቡ ሁለት አሽከርካሪዎች የእጅ ማፍታቻ ሥልጠና በአንበሣ አውቶብስ ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፣
- ለግሪን ኤሪያው መከለያ የሰንሰለት አጥር ሥራ ተሰርቷል፣
- ተጨማሪ የፅዳትና የጥበቃ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል፣
- ከኮተቤ ግቢ በርካታ ንብረቶች ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ወደ መገናኛ አዲሱ ህንፃ እንዲጓጓዙ ተደርጓል፡፡
- ለሚወገደው ተሽከርካሪ ከአሽከርካሪ ባለሥልጣን የመጣውን የሞዴል ቁጥር ማስተካከያ መረጃ በማምጣት ለመንግስት ግዥ እንዲደርስ ተደርገዋል፡፡ ልዩ ልዩ ንብረቶችን የአዳራሽ፣

የካፍቴርያ ፣ የተፈቱ አሉሚኒየሞች፣ የተለያዩ ሥራ ክፍሎችና የሜቴክ በርካታ ማሽኖች ተንገዝው መገናኛ በተዘጋጀላቸው ቢሮ እንዲገቡና እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አዲስ የፅዳት አገልግሎት ውል ተፈፅሟል (ክንውን 100%)፡፡

**10.3 የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ** (ክንውን 100%)፡፡

10.3.1 ለነባር ሲሰተሞችን (ኢፍሚስ፣ኢጂፒ፣ ኢስሚስ፣ ኢሜል፣ዌብሳይት እና ዌብ ፖርታል) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ

- በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ለሁሉም የስራ ክፍሎች የጠያቂና አጽዳቂ (role)፣ ፋይናንስ ላይ ላሉ ባለሙያዎች፣ መሰረታዊ ላይ ላሉ ባለሙያዎች ከፋይናንስ ስራ አስፈጻሚ በቀረበው ጥያቄ መሰረት በድምሩ 128 የኢፍሚስ እና ኢጂፒ አካውንት የማስተካከል ስራ፡
- የተጠቃሚዎች የይለፍ ቃላቸውን ለረሱ ባለሙያዎች የአካውንት ሪሴቲን (Account resetting) የ39 የተጠቃሚዎች የይለፍ ቃል ሪሴት የማድረግ ስራ ተከናውኗል (User Password resetting)
- ለሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቢሮዎች የኔትወርክ ዝርጋታ እና 3 ኮምፒውተር እና የአንድ ፕሪንተር ጥገና ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

10.3.2 የኢንስቲትዩቱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ

- የኢንስቲቲዩቱን የኔትወርክ መሰረተ ልማቶች ደህንነት በየቀኑ የመጠበቅ፤
- ከኔትወርክ እና ከኢንተርኔት ጋር ተያይዞ ከተጠቃሚዎች የሚቀርቡ የቴክኒክ ድጋፎችን የመስጠት ስራ ፤
- የአዲሱ ህንጻዎች ኔትወርክ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ስራዎች እንዳይስተጓጎሉ ወሳኝ የሆኑ ሶስት ስራ አስፋጻሚዎች ኔትወርክ እንዲያገኙ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**10.4 የተቋማዊ ለውጥ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት** (ክንውን 97.86%)፡፡

10.4.1 የተቋማዊ ለውጥ አሰራር ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር በምርጥ ተሞክሮ የተገኙ ውጤቶችን በመጠቀም የተቋማዊ ለውጥ አመራር ማንዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ ከውጪ ሁለት ተቋማት ጉብኝት አድርገን ከዚሁ በመነሳት የማንዋል ዝግጅት 95% ተጠናቋል (ክንውን 95%)፡፡

10.4.2 የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት እንዲፈቱ ለሚመለከተው በማቅረብና እርምጃ ለማስወሰድ ታቅዶ የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት እንዲፈቱ የሚረዳ ፎርሞችን አሻሽለን በመቅረፅ በተገልጋዮች እንዲሞሉ በማድረግ ለቀረቡ አስተያየቶችና ቅሬታዎች በሚመለከተው ክፍል በወቅቱ ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል (ክንውን 100%)።

**ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** (ክንውን 100%) ።

**11.1 ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ** (ክንውን 100%) ።

11.1.1 ከመንግስት በጀት የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመከታተል ታቅዶ

- በመንግስት የተፈቀደልን ካፒታል በጀት የሀገር ውስጥ ግዥ ተጠናቋል የኢንተርናሽናል ግዢ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል በመፈጸም LC ተከፍቷል (ክንውን 100%)።

11.1.2 በዓለም ባንክ ብድር የተገዙ አዳዲስ የላቦራቶር መሳሪያዎችን እና ከቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ መሳሪያዎችን በመከታተል ወደ ስራ በማስገባት ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ

- የሙቀት፣ የጨረራ፣ የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ የላቦራቶር መሳሪያዎች እና ከኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ የኤሌክትሪካል ጊዜና ድግግሞሽ የላቦራቶር መሳሪያዎችን በመከታተል ወደ ስራ ተገብቷል።
- ለላቦራቶሪ መሳሪያዎች ገጠማ የሚዉሉ 14 ቤንቾች ገጠማ ተጠናቋል በዝርዝር መስፈርቱ መሰረት ተገምግሞ ጉድለቶቹ እንዲሟሉ አቅራቢዉ ተጠይቋል።
- የኬሚካል ሥነ-ልክ ምርምር ላቦራቶሪ መሳሪያዎች ገጠማ የሚዉሉ የጎደሉ ተጨማሪ ኬሚካሎችና UPS የኬሚካል ለቦራቶሪ ገብተዉ Organic inorganic ላቦራቶሪ የኬሚስትሪ የአናሊትካል መሳሪያዎች ገጠማ እየተከናወነ ይገኛል።
- የprimary pH standard መሳሪያዎች ገጠማ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቶ ባለሙያዎች ለገጠማ ኢንዲመጡ ተጠይቋል። ለዚሁ ሥራ ሚያገለግሉ auxiliary equipment እና ኬሚካሎች መሳሪያዉን የሚገጥሙት ባለሙያዎች በጠየቁት መስፈርት መሰረት ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ ግዥዉ ተከናዉኗል።
- ተጨማሪ የጎደሉ ባለ 20 KVA እና ባለ 10 KVA UPS ግዥዉ ተከናዉኗል። እንዲሁም አኮስቲክና ቫይቪሬሽን ከዉጪ በመጡ ባለሙያዎች ኢንስቶል ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል (ክንውን 100%)።

**11.2 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** (ክንውን 100%) ፡፡

11.2.1 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው ለመፈራረምና ለመመዘን ታቅዶ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በየደረጃው የመፈራረም ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የ2016 በጀት ዓመት እና የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት ውጤት ተኮር ምዘና ተከናውኗል (ክንውን 100%) ፡፡

## 4. ዓበይት ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎኖች

**ጠንካራ ጐኖች**

- በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በ4 ላብራቶሪዎች ማስመዝገብ መቻሉ፡፡
- በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሣይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ የጽንሰ ሀሳብ እና የተግባር ስልጠናዎች መሰጠቱ
- በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት በጅማ እና ባህር ዳር ቅርንጫፍ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመሩ
- በሥነ-ልክ ዘርፍ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ መቻሉ፣
- በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨቱ
- ዕዉቅና በተገኘባቸዉ እና ባልተገኘባቸው የአለካክ መስኮች የውስጥ የጥራት ኦዲት መከናወኑ
- በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር መቻሉ
- የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት መቅረቡ፤

**ደካማ ጐን**

- ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት አለመቻሉ
- በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠና ማግኘት አለመቻሉ

## 5. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሲስተም መቆራረጥ እና አገልግሎት አለመስጠት፤
- የሰለጠኑ ባለሙያዎች መልቀቅ እና ቅጥር አለመፈቀድ፤
- የተሽከርካሪ እጥረት
- የበጀት እጥረት

**የተወሰዱ መፍትሔዎች**

- ለግዢ ኤጀንሲ በደብዳቤ በተደጋጋሚ በማሳወቅ ምላሽ እየተጠበቀ ነው፡፡
- ቅጥር እንዲፈቀድልን የሚመለከተውን አካል ለማስፈቀድ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ገ/ሚ ለማስፈቀድ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡
- በተደጋጋሚ ተጨማሪ በጀት ገንዘብ ሚኒስቴር በማስፈቀድ ለመፍታት ተሞክሯል፡፡

## 6. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ተግባራት

- የሰው ኃይል ማሟላት
- የንጽጽር ፕሮግራሞች ተሳትፎን ለማሳደግ የሚያስችሉ ክትትሎችን ማጠናከር ፤
- አዳዲስ ክልሎችን በህጋዊ ስነልክ ዘርፍ ድጋፎችን ለማድረግ የሚሰሩ ስራዎችን በፍጥነት መከወን፤

## 7. የ2017 በጀት ዓመት የሰው ኃይል መረጃ ሪፖርት

| ተ.ቁ | የሠራተኞች የት/ደረጃ | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | | | በ2017 በጀት ዓመት ውስጥ አዲስ የተቀጠሩ | | | በ2017 በጀት ዓመት ውስጥ የለቀቁ | | | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | 1ኛ-12ኛ | 14 | 21 | 35 | - | - | - | 2 | 2 | 4 | 12 | 19 | 31 |
| 2 | TVT (Level) | 5 | 13 | 18 | - | - | - | 1 | - | 1 | 4 | 13 | 17 |
| 3 | ዲኘሎማ (10+3) | 9 | 5 | 14 | - | - | - | - | - | - | 9 | 5 | 14 |
| 4 | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 76 | 45 | 121 | 4 | - | 4 | 9 | 3 | 12 | 70 | 42 | 112 |
| 5 | ኤም.ኤ/ኤም.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 25 | 7 | 32 | - | - | - | - | 1 | 1 | 26 | 6 | 32 |
| 6 | ፒ.ኤች.ዲ | 1 | - | 1 | - | - | - | - | - | - | 1 | - | 1 |
| ድምር | | 130 | 91 | 221 | - | - | - | 12 | 6 | 18 | 122 | 85 | 207 |

| 8. የ2017 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈጻጸም | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ | | በ2017 በጀት ዓመት ላይ የዋለ/ወጪ | | በ2017 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ከበ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር |
| | ከመንግስት | | ከመንግስት | ከውጭ እርዳታ | |
| ፕሮግራም 01 | 103,908,475 | | 102,272,8516.61 | | 99.38 |
| ፕሮግራም 02 | 21,739,146 | | 21,976,117.17 | | 100 |
| ፕሮግራም 03 | 15,390,762 | | 15,390,762 | | 98.9 |
| ፕሮግራም 04 | 13,487,338 | | 13,080,333.8 | | 96.9 |
| *መደበኛ ድምር* | *154,525,721* | | 153,561,337 | | 99.38 |
| *ካፒታል በጀት* | *70,518,250.0* | | 70,515,375.00 | | *99.9* |
| ድምር | 225,043,971 | | 224,076,712.26 | | 99.57 |

### 9. ማጠቃለያ

የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ (2017-2018) መሰረት በማድረግ ፣የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማካተት የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም በመገምገም እና የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ ፣ ስጋትን በመተንተን ፣ 11 ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማካተት፣ በዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራት በማካተት የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ተከልሶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል ፡፡እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ስርዓትን ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 207(ወ=122, ሴ=85) ሠራተኞችን ይዞ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሁለት የጥናት እና ምርምር ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ Completion of the Review by Implementation in Excel of mass calibration using orthogonal design ጥናት ተጠናቋል፡፡ በቮልቴጅ መዋዠቅ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚታደግ ዲቫይስ ቅድመ ፕሮቶታይፕ ፍተሻ ተጠናቆ በሙከራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ከማሳደግ አንጻር ለ 31,538 የመለኪያ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ282 ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ8 ተቋማት በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የዉስጥ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ተከናውነዋል ፡፡

ለኢትዮጵያ ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራዝ ፣ ለኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ፣ለምርምር ስልጠና ማእከል የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ ተቋማት በጥያቄያቸው መሰረት 100% የቴክኒክ፣ የድጋፍ እና የምክር አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡

ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት አንጻር ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል፡፡ በውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ በሙቀት እና በኤሌክትሪካል ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ጊዜያቸዉ የደረሰ ማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡

የአለካክ ወሰኖችን ከማሳደግ አንጻር በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ላይ የስልጠና ቢጋራ (TOR) ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በcentrifuge calibration ላይ በራስ ባለሙያ ስልጠና በመስጠት ስራ ተጀምሯል። እንዲሁም በፎቶሜትሪ /photometer/ የአለካክ መስክ ስልጠና በመዉሰድ የካሊብሬሽን አገልግሎት ተጀምሯል።

ማህበራዊ አገልግሎት በተመለከተ ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት 18,735.59 ብር ድጋፍ ተደርጓል። በተጨማሪም ደመዎዛቸው አነስተኛ ለሆኑ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ከሠራተኛ ክበብና ከሌሎች ሠራተኞች በማስተባበር ለአዲስ ዓመት የዱቄትና ዘይት ድጋፍ ተደርጓል። እንዲሁም ለመቅዶንያ አረጋውያን መረጃ 93,750 ብር ማዕድ የማጋራት ስራ ተሰርቷል::

በ2017 በጀት ዓመት ውስጥ ብር 15,018,152.28 የአገልግሎት ክፍያዎች ተሰብስቦ ለገ/ሚ ገቢ የተደረገ ሲሆን የ2017 በጀት ዓመት የተግባር አፈጻጸም 94.5% ሲሆን የበጀት አፈጻጸሙ 99.5% ሆኗል።

## 10. የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| ግብ 1 | የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ | | | | | |
| 1.1 | **ጥናትና ምርምር ማካሄድ (ክብደት 4)** | | | | | |
| 1.1.1 | ጥናትና ምርምር ማካሄድ | 0 | 2 | 2 | 1.9 | 95 |
| 1.2 | የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.2.1 | ለ34000 ዓለም ዓቀፍ ትስስር የጠበቀ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | 24854 | 34000 | 34000 | 31538 | 92.76 |
| 1.3 | የጥገና (የቴክኒክ አገልግሎት ) መስጠት አገልግሎቶች | | | | | |
| 1.3.1 | ለ350 ተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና(የቴክኒክ) አገልግሎት መስጠት | 252 | 350 | 350 | 282 | 80.6 |
| 1.4 | **የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት (ክብደት 4.5)** | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች ስልጠና መስጠት | 6 | 8 | 8 | 8 | 100 |
| 1.5 | **የቴክኒክ ድጋፍ እና ምክር አገልግሎቶች መስጠት (ክብደት 6)** | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለግል ባለሃብት፣ ለህጋዊ ሥነ-ልክ፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ የግል ባለሃብት ወ.ዘ.ጥያቄ ለሚያቀርቡ 100% የቴክኒክ እና የምክር አገልግሎቶች መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት (ክብደት 1.5)** | | | | | |
| 1.6.1 | ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ ለሚጠይቁ ደንበኞች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 0 | 0 |
| 1.7 | የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 1.7.1 | የውጭ ተገልጋይ እርካታ ጥናት ማድረግ | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 2 | ተደራሽነትን ማሳደግ | | | | | |
| 2.1 | | | | | | |
| 2.1.1 | በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት በጅማ እና ባህር ዳር ቅርንጫፍ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር፡፡ | 0 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 2.2 | **የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ** | | | | | |
| 2.2.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀት፣ መጫንና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 2.2.2 | ለዌብሳይት ተጠቃሚዎች ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 2.3 | **የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት** | | | | | |
| 2.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ለማስጨበጫ ፕሮግራሞች ማካሄድ | 2 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| ግብ 3 | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | | | | | |
| 3.1 | የበጀት አጠቃቀምን መከታተል | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በእቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | 94 | 100 | 100 | 99.5 | 99.5 |
| 3.2 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | | | | | |
| 3.2.1 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | 13 ሚሊዮን | 15 ሚሊዮን | 15,000,000 | 15,018,152.28 | 100 |
| 3.3 | **የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** | | | | | |
| 3.3.1 | የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት | 5 | 6 | 6 | 6 | 100 |
| ግብ 4 | **የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 4.1 | **ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ** | | | | | |
| 4.1.1 | አጋር ድርጅቶችን ስትራቴጂካዊ አስተዋጽኦ ለማሳደግ ፕሮጀክቶች መቅረጽ | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| **ግብ 5** | **አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** | | | | | |
| 5.1 | **ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማስራጨት (ክብደት )** | | | | | |
| 5.1.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ፣ | 2 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 5.1.2 | በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስራጨት:: | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 5.2 | **ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል** | | | | | |
| 5.2.1 | ዕዉቅና በተገኘባቸዉ (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን | 0 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 5.2.2 | ዕዉቅና ባልተገኘባቸው የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ እና ማስተካከያዎችን ማከናወን | 0 | 8 | 8 | 8 | 100 |
| 5.2.3 | በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የተቋረጡ የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት እና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ማድረግ፣ | 0 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 5.2.4 | በሁሉም ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች የግዝፈት እና የሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን፣ | 5 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 5.2.5 | የውስጥ ጥራት ኦዲት በተካሄደባቸው የአለካክ መስኮች በ ISO/IEC 17025 የጥራት ሥራ አመራር የአሰራር ሥርዓት መሰረት የስራ አመራር ግምገማ /Management Review/ ማካሄድ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 5.2.6 | በተካሄደው የውስጥ ጥራት ኦዲት ግኝት መሰረት የእርምት እርምጃ መውሰድ እና ማስተካከያዎችን በማከናወን ሪፖርት ማቅረብ፣ | 2 | 2 | 2 | 2 | 100 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 5.3 | **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** (ክንውን 58%)። | | | | | |
| 5.3.1 | ከ ጀርመን እውቅና ሰጭ ተቋም (DAkkS) በተገኘ የሚዛን ካሊብሬሽን እውቅና መሰረት ለሁለት ቅርንጫፍ ላቦራቶሪ ሰራተኞች የ Competency training በመስጠት እና በማብቃት ዓለም ዓቀፍ አውቅና ያለው የካሊብሬሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል። | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 5.3.2 | በቀጣይ ዓለም አቀፍ ዕውቅና የሚጠየቅባቸው (የጨረራ፣ የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እና የኬሚካል) የአለካክ መስኮች የልኬት ወሰን መለየት | 0 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| 5.4 | በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ (ክብደት 4) | | | | | |
| 5.4.1 | በኤሌክትሪካል የአለካክ መስክ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ማድረግ | 2 | 2 | 2 | 3 | 150 |
| 5.4.2 | በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያለ በይዘት ለማስመዝገብ ክትትል ማድረግ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 5.5 | **ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ** | | | | | |
| 5.5.1 | AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | |
| 5.6.1. | የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት አደረጃጀት ለዉጥ ምክንያት በISO 17025:2017 የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት Quality manual ለመከለስ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| **ግብ 6** | **የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| | | | | | | |
| 6.1 | **የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ (ክብደት 6)** | | | | | |
| 6.1.1 | በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ የካሊብሬሽን ስራ ማስጀመር እና የቅድመ ዕውቅና ስራዎችን መስራት፣ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 6.1.2 | በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር | 0 | 4 | 1 | 1 | 33.33 |
| 6.1.3 | በኬሚካል ሥነ-ልክ ዘርፍ Reference materials production, primary pH standard and Electrocondactivity lab የጽንሰ ሀሳብ እና የተግባር ስልጠና ማግኘት | 0 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 6.1.4 | በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር | 0 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| **ግብ 7** | **የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** | | | | | |
| 7.1 | **የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክብደት 1) | | | | | |
| 7.1.1 | የኢንስቲትየዩቱን የካሊብሬሽን አገልግሎትን የኦንላይ አገልግሎት በከፊል ተግባራዊ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ለድረግ | 0 | 2 | 2 | 0.6 | 30 |
| 7.1.2 | የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት በከፊል ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል | 0 | 1 | 1 | 0.95 | 95 |
| 7.1.3 | የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 0 | 4 | 3 | 1.8 | 80 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 7.2 | **ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ (ክብደት 1.5)** | | | | | |
| 7.2.1 | በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ማስጠበቅ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.2 | ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ | 100 | 100 | 100 | 0 | 0 |
| 7.3 | **የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** | | | | | |
| 7.3.1 | በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ማጠናቀቅ | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 7.4 | **የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** | | | | | |
| 7.4.1 | በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 8 | **ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** | | | | | |
| 8.1 | | | | | | |
| 8.1.1 | እስከ 32 ለሚደርሱ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለሚመጡ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 8.2 | ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | | | | | |
| 8.21 | በኬሚካል ስነ-ልክ የአለካክ መስክ በReference materials production ከ(NMISA) and primary pH Standards ከKRISS laboratories ጋር ስራ የማስጀመር ስራዎችን መስራት፣ | 0 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 8.3 | **ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| | (ክብደት 0.5) | | | | | |
| 8.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| ግብ 9 | የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ | | | | | |
| 9.1 | የሰው ሀብት ልማት ማልማት | | | | | |
| 9.1.1 | ሠራተኞች ስልጠና መስጠት | 151 | 125 | 125 | 189 | 100 |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | 2 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 9.2 | የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | 19495 | 19560 | 19560 | 18735.59 | 95.8 |
| 9.2.2 | ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶችን በማፈላለግ የተቋሙን ሴቶች ተጠቃሚ ማድረግ | 0 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 9.3 | የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ (ክብደት 2.5) | | | | | |
| 9.3.1 | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የስነምግባር መመሪያ ማጠናቀቅ፣ | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 9.3.2 | በተቋሙ በህግ ሀብት ማስመዝገብ የሚገባቸው ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ መከታተል፣ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ግብ10. | የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል | | | | | |
| 10.1 | የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ (ክብደት 1) | | | | | |
| 10.1.1 | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 10.2. | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 10.2.1 | የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ማድረግ (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ እና እድሳት) | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3 | የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ (ክብደት 4) | | | | | |
| 10.3.1 | ለነባር ሲስተሞችን (ኢፍሚስ፤ ኢጺፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 10.3.2 | የኢንስቲትዩቱነን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 10.4 | **የተቋማዊ ለውጥ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት (ክብደት 3.5)** | | | | | |
| 10.4.1 | የተቋማዊ ለውጥ አሰራር ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር በምርጥ ተሞክሮ የተገኙ ውጤቶችን በመጠቀም የተቋማዊ ለውጥ አመራር ማንዋል ማዘጋጀት | 1 | 1 | 1 | 0.95 | 95 |
| 10.4.2 | የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት እንዲፈቱ ለሚመለከተው በማቅረብና እርምጃ ማስወሰድ | 1 | 1 | 1 | 2 | 100 |
| 11 | **የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** | | | | | |
| 11.1 | **ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ (ክብደት 2)** | | | | | |
| 11.1.1 | ከመንግስት በጀት የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም መከታተል | 0 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 11.1.2 | በዓለም ባንክ ብድር የተገዙ አዳዲስ የላቦራቶር መሳሪያዎችን እና ከቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ መሳሪያዎችን በመከታተል ወደ ስራ በማስገባት ሪፖርት ማቅረብ | 0 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 11.2 | **የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** | | | | | |

| | | | | የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረምና መመዘን | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |